# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703

ቀን፡- ጁን 28፣ 2018

**በወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ**
**ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግለጫ**

በሀገራችን ኢትዮጵያ እየታየ ያለው ሀገራዊ መግባባት የመፍጠር እንቅስቃሴ እንዲሁም በአካባቢያችን ሰላም ለማምጣት ከኤርትራ መንግስት እየተደረገ ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግኑኝነት መጀመር ያለንን ላቅ ያለ አድናቆት እናቀርባለን። ነገር እነዚህ እየተመዘገቡ ያሉትን ድሎች መጥፎ ጥላ የሚያጠላ እና ሀገራችንን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ሊወስዱ የሚችሉ ክስተቶች መፈጠራቸው በእጅጉ አሳስቦናል አሳዝኖናል። የንጹሀን ዜጎች ህይወት በከንቱ እያለፈ በተለያዩ የሀገራችን አከባቢዎች ተንቀሳቅሰው ለመኖር እና ሰርተው ንብረት ለማፍራት የቻሉ ዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ጥቃት እየደረሰባቸው ነው። ለምሳሌ ያህል በሐዋሳ ከተማ በወላይታ ተወላጆች የደረሰ ግድያ እና ማፈናቀል፤ በባቲ ከተማ በድጋፍ ሰልፍ ስም በትግራይ ተወላጆች ንብረት የመዝረፍ እና ህይወት የማጥፋት ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። መንግስት የዜጎች ደህንነት የመጠበቅ ሐላፍነት ብቻ ሳይሆን ግደታም አለበት። በመኾኑም መንግስት እነዚህን ጥቃቶችን በአፋጣኝ እንዲያስቆም እና የሕግ የበላይነት እንዲያሰፍን ጥሪያችን እናቀርባለን።

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ ማእከላዊ ጽ/ቤት